በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 5

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

**ግንቦት ፲፭ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም.**

# የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

- **የዛሬው ትምህርታችን ማዕከል ጥንታዊና ጥንታዊውን ያልሆኑ የክርስቲያን ቤተሰቦች ሕይወት መመልከት ነው። ትዳራችን ጥንታዊ ገጽታ ያለው እንዲሆን እንሻለን ወይስ ጥንታዊ ያልሆነ ገጽታ ያለው?**
- **በዚሁ ትምህርት የወንድና የሴትን ድርሻ፣ በትዳር ሕይወት ስላለ መሪነት/መጋቢነት፣ ወንድነት ወይም ሴትነት ምን እንደሆነና በምን እንደሚገለጽ፣ በትዳር ሕይወት ወሳኙ ማን እንደሆነ... በእግዚአብሔር ፈቃድ እንማራለን።**

<u>የወንድና የሴት ድርሻ</u>

I. ***<u>ጥንታዊ ቤተ ሰብ</u>***

1. ወንድ
    - ራስ (መሪ) ነው። በእርግጥ እውነተኛው የሁሉ መሪ ክርስቶስ ነው።
    - ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ሰጪ መጋቢ ነው። ፍቅር፣ የልጆች አስተዳደግ...
    - ባል ነው።
    - አባት ነው።
2. ሴት
    - ሚስት ናት።
    - የቤት እመቤት ናት። የቤቱ ሥራ የሚበዛው የርስዋ ነው... ወንድ ማዕድ ቤት ቢገባ እንደ ነውር ይታሰባል...
    - እናት ናት።

II. የ"ኢንዱስትሪ አብዮት" ሠራተኞች እናቶችን ፈጥሯል። ይህም የቤተ ሰብንና የትዳር ሕይወትን መልክ ቀይሮ ጥንታዊ ገጽታው ሌላ መልክ እንዲይዝ አድርጎታል።

# የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

III. ***ዘመናዊው  ወይም ጥንታዊ ያልሆነው ቤተ ሰብ***

1. ወንድ
    - ራስ (መሪ) ነው፡፡ በእርግጥ እውነተኛው የሁሉ መሪ ክርስቶስ ነው፡፡
    - ሰጪ ነው፡፡
    - ባል ነው፡፡
    - አባት ነው፡፡
    - የቤት ሥራ ይሠራል፡፡ ጥገና፣ አናጢነት፣ ልብስን መተኮስ … ልጆችን ይንከባከባል፣ ልብስ ያጥባል፡፡
2. ሴት
    - ራዳት መሪ ናት፡፡ ልክ እንደ ረዳት አውሮፕላን አብራሪ…
    - ሰጪና ሠራተኛ ናት፡፡
    - ሚስት ናት
    - የቤት እመቤት ናት፡፡
    - እናት ናት፡፡

- ለእኛ ትዳር የሚሠራው የቱ ነው? ጥንታዊው ነው ወይስ ጥንታዊ ያልሆነው? ሳያውቁ ሁለቱን ማቀላቀል ወይም ማደበላለቅ አደጋ ያስከትላል፡፡

# የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

IV. የጋብቻ ዓይነቶች

1. ቋሚ (መንፈሳዊ/እውነተኛ)፡- ትክክለኛው የትዳር ዓላማና ግብ ላይ አትኩሮት ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ በትዳሩ ቀዳሚው እግዚአብሔር ነው፣ የሚከተሉትም ሚስት/ባል፣ ልጆች፣ ወላጆች… ወዳጆች፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት፣ ወዳጆቻችን… እዚህ ላይ የ“ሕንድ” ፊልም ላይ የምናያቸው ዓይነት መንገዶች አይሠሩም…
2. ቁሳዊ፡- ገቢን፣ ወጪን፣ ወዘተን ይመለከታሉ… ውጤቱም መድረቅ መበስበስ መቀጨጭ ነው፡፡

- ስለዚህ የሚቀድመውን ቋሚውን ማስቀደምና ከቁሳዊውም የሚካተቱትን ማወቅና መለየት ይኖርብናል፡፡

V. መሪነትና ራስን መስጠት

I. ልብና አንጎል

- “ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፥ የሴትም ራስ ወንድ፥ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልታውቁ እወዳለሁ። ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለ ሆነ ራሱን መከናነብ አይገባውም፤ ሴት ግን የወንድ ክብር ናት። ነገር ግን በጌታ ዘንድ ሴት ያለ ወንድ ወንድም ያለ ሴት አይሆንም። ሴት ከወንድ እንደ ሆነች እንዲሁ ወንድ ደግሞ በሴት ነውና፤ ሁሉም ከእግዚአብሔር ነው።” <u>*ቀዳ ቆሮ 11፡3፣7፣11፣12፡፡*</u>
- ሴት የተገኘችው ከወንድ ከአዳም ነው፣ አዳም ሰውም የተገኘው ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ይህም ባርነትን አያመለክትም፡፡ ባል ከእርሱ ለተገኘችው ለሚስቱና ለልጆቹ ኃላፊነት አለበት፡፡ የከበደውንና ከአቅሙ በላይ የሆነውን ወዳስገኘው ወደ እግዚአብሔር ያቀርብና መፍትሔ ያገኝበታል፡፡
- “ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ። ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና። ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ። ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤…

# የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

… እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል።" *ኤፌ 5፡21-29።*

- ከላይ በተጠቀሰው የመጽሐፍ ክፍል የሴቶች ድርሻ ሦስት የወንዶቹ ደግሞ በርከት ብሎ ስድስት ነው።
- ራስነት አንዱን ትልቅ ሌላውን ታናሽ አያደርግም። በምስጢረ ተክሊል ሲጋጠሙ እያንዳንዳቸው ሙሉ ይሆናሉ። እርሱ ያለርሷ እርሷም ያለርሱ ጎዶሎ ናቸው።
- ባልና ሚስት በእግዚአብሔርም በልጆቻቸውም ፊት በትዳር እኩል ቢሆኑም በተሰጣቸው ድርሻ ግን ይለያያሉ።
- "ሚስቶች ሆይ፥ በጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ ተገዙ። ባሎች ሆይ፥ ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው።" *ቆላ 3፡18-19።*
- "እንዲሁም፥ እናንተ ሚስቶች ሆይ፥ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ፥ በፍርሃት ያለውን ንጹሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው። ለእናንተም ጠጉርን በመሸረብና ወርቅን በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናጸፍ በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ።… እንዲሁም፥ እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው።" *ቀዳ ጴጥ 3፡1-4 እና 3፡7።*
- ቅዱስ ጴጥሮስ ባለትዳር ነበር… ሚስቶችን መንፈሳዊ ኑሮአችሁን አሳዩ ሲል ባሎችን ደግሞ መራር አትሁኑባቸው ብሎአል።

# የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

II. ወንድነትና ሴትነት

- ወንድ የበላይ ሴትን የበታች አድርጎ ማሰብ (Chauvinism) እና ለሴቶች ከፍ ያለ መብትና ጥበቃን ስለማድረግ መቆም (Feminism)
- ወንድነት የሚሰማት ሴት እና ደካማ ወንድ
- ጾታን መቀየር

1. ወንድነት
   - የወንድነት መለኪያ ያልሆኑ ነገሮች
     1. ጩካኝ፣ ጩኸታም በጡንቻውና በድምጽ ማስፈራራት
     2. ስንፈተ ወሲብ
     3. ሌሎችን ልቆጣጠር ማለት
   - የሚሆናቸው ነገሮች
     1. ራስን መቆጣጠር
     2. ጀግና፦ አይጥ ሲያይ መውጫ ቀዳዳ የሚፈልግ መሆን አይጠበቅበትም…
     3. ትሑት

# የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

4. ርኅሩኅ
5. የሚገጥሙትን ነገሮች ተጋፍጦ የሚወጣ
6. በማኅበራዊ ሕይወቱ ጠንካራ የሆነ
7. እምነት የሚጣልበት
8. ኃላፊነት የሚሰማው
9. ቅን መሪ
10. የማይለዋወጥ ጽኑ አቋም ያለው
11. ወሳኝ ወይም በነገሮች ላይ መወሰን የሚችል
12. የማይነዋወጥ - የመጣ ነፋስ የሚያወዛውዘው ያልሆነ

2. ሴትነት
    - የሴትነት መለኪያ ያልሆኑ ነገሮች
        1. መጥፎ ነገር እንዲሠራ አሳሳች መሆን
        2. የተምታታ ደካማነት፡- እንዲታዘንላቸው ደካማ መስሎ መታየት
        3. የወንዴነት ጠባይ፡- እንደ አማዞን ደሴት ሰዎች ሆኖ መገኘት፣ እኔ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ ወንድ ባል አያስፈልገኝም… ማለት
        4. ማወክ ወይም መበጥበጥ
        5. ጨካኝነት
        6. ጨኽታምነት

# የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

- ሴት የምትሆናቸው ነገሮች፡- ቅዱሳት አንስትን የሚመስሉላቸውን ሁሉ መያዝ ይገባል።

   1. ንጽሕና
   2. ቅድስና
   3. ጥበበኛ
   4. ትሕትናን የተላበሰች ውብ
   5. ቅን
   6. ጸጥተኛና ዝግ ያለች
   7. ርኅሩኅ
   8. አፍቃሪና ተግባቢ
   9. እናትነት

III. ክርስቲያናዊ መሪነት

- ፈላጭ ቆራጭነት አምባ ገነንነት የሌለበት ነው።

1. እምነት የሚጣልበት (መግባባት፣ መረዳዳትና ሥራዎችን ተግባብቶ መከፋፈል)
2. ትዕግሥት ያለበት። "ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም።" ***ቀዳ ቆሮ 13:4።***
3. ያግዛል፣ ያበረታታል። "ወንድሞች ሆይ... ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው፤ ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው፤ ለደካሞች ትጉላቸው፤ ሰውን ሁሉ ታገሡ።" ***ቀዳ ተሰ 5:14።***

# የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

4. **ጥበበኛና ማስተዋልን ገንዘብ ያደረገ ነው፡፡** “ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ፡፡ … ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል፡፡… ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ፡፡” ***ኤፌ 5:26-27፣ 30፣33፡፡***
5. **መጋቢ ተንከባካቢ ነው፡፡** ***ኤፌ 5:29፡፡***
6. **ንቁ ነው ለሁሉ ይጠነቀቃል፡- አእምሮውና አካሉ፡፡**
7. **ታማኝነትና ትሕትናን የያዘ ነው፡፡**
8. **መሥዋዕትነት አለበት፡፡** “ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፡፡” ***ኤፌ 5:25፡፡***
9. **መንፈሳዊ ነው፡፡** “በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ፡፡” ***ኤፌ 5:26-27፡፡***
10. **ራስን ዝቅ በማድረግ የሚያገለግል ነው፡፡** “እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል፡፡” ***ዮሐ 13:14***

# የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

IV. ራስን መስጠት ማለት

1. ክብር መስጠት
2. አድናቆት
3. መፍራት
4. ከፍ ማድረግ
5. ራስን መግዛት
6. ማመስገን
7. ማገዝ፡- ድልድይና የተሸከመውን ምሰሶ አስቡ… ምሰሶ ባይሸከመው ድልድይ አይቆምም፡፡ የምሰሶው መሰበር የድልድዩ መፍረስ ምንጭ ይሆናል፡፡ ምሰሶው ለድልድዩ ድልድዩም ለምሰሶው አስፈላጊ ናቸው፡፡
8. ማክበር
9. መስጠት
10. አብልጦ ማድነቅ ወዘተ ነው እንጂ ባርነት አይደለም፡፡

# የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

V. በቤተ ሰባዊ ሕይወት ውሳኔ ሰጪ ማነው?

- ክርስቲያናዊ ቤተ ሰቦች ሁለቱም ተማክረው ተስማምተው ይወስናሉ።
- ከባድና ቀላል ውሳኔዎችን መወሰን ቢያስፈልገን ወንዶች የትኛውን ትመርጣላችሁ? ሁለቱንም? ሴቶችስ? ሁለቱንም?
- እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የምንኖርና ትዳራችንም በክርስቲያናዊ ሥርዓት የሚመራ ከሆነ ባል ነኝና ብቻዬን ወሳኝ መሆን አለብኝ የሚል አይኖርም።
- መግባባት ስላልቻልን… እኔ ወንድ ስለሆንኩ እወስናለሁ… አይፈቀድም። በግድ ሚስቶቻችሁን አስጨንቃችሁ ብናደርገው እንኳ አንድ ቀን የሚያስከትለውን መጥፎ ውጤት እናጭዳለን።
- የእግዚአብሔር ዕቅዱ ሁለቱም ዋጋ ሥፍራ አላቸው የሚል ነው። ስለዚህ በትዳር ውሳኔ የሚወሰነው በሁለቱም (በባልና በሚስት) ስምምነት ነው።

For your quesries E-mail:
kesisolomon3@gmail.com

To get all lessons surf :
www.zeorthodox.org

... ክፍል ስድስት ይቀጥላል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።